መመርያ ቁጥር 149/2016

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፤ ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በአዲስ አበባ ከተማ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓታት ላይ ለሚታየው ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅና አደጋ እንዲሁም የከባቢ አየር ብክለት የደረቅና ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችና የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች አስተዋጽዖ የጎላ በመሆኑ እነዚህ ተሽከርካሪዎች ወደ ከተማዋ መግባት የሚችሉበትንና በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ሰዓት በመወሰን ችግሮቹን መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በሰዓት መገደቡ ፍሰቱን ከማሳለጡም በተጨማሪ በዚህ መመሪያ እንቅስቃሴያቸው የተወሰነላቸው ተሽከርካሪዎችም አገልግሎታቸውን በተቀላጠፈና ወጪን በሚቀንስ መልኩ ማከናወን እንዲችሉ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፣ ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 38/2013 ላይ የሚስተዋሉ ለአፈፃፀም እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ለመቅረፍ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 149/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **“ከተማ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
3. **“ባሥልጣን”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ነው፤
4. **“መንገድ”** ማለት ተሽከርካሪዎችና እግረኞች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ መንገድ ወይም መተላለፊያ ነው፤
5. **“ትራፊክ”** ማለት በማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ መንገድ ላይ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚነዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፤
6. **“የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ”** ማለት ከ1 ቶን /10 ኩንታል/ በላይ የሆነ የመጫን አቅም ያለው በከተማው መንገድ ላይ የሚሄድ ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራ ባለሞተር፤ ተሳቢ ያለዉ ወይም ተሳቢ የሌለው ተሽከርካሪ ሲሆን ማናቸዉንም የደረቅ እና ፈሳሽ ቀላል፤ መካከለኛ እና ከባድ የጭነት ተሽከርካሪን ይጨምራል፤
7. **“ቀላል የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ”** ማለት የመጫን አቅማቸው ከ10 ኩንታል በላይ ሆኖ እስከ 25 ኩንታል ወይም ከ1ቶን በላይ ሆኖ እስከ 2.5 ቶን የሆኑ በከተማ ዉስጥ በደረቅ እና ፈሳሽ ጭነት ላይ የተሰማሩ የንግድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤
8. **“መካከለኛ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ”** ማለት የመጫን አቅማቸው ከ25 ኩንታል እስከ 35 ኩንታል ወይም ከ2.5ቶን እስከ 3.5 ቶን የሆኑ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤
9. **“ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ”** ማለት የመጫን አቅማቸው ከ35 ኩንታል ወይም ከ 3.5 ቶን በላይ የሆኑ ባለተሳቢና ተሳቢ የሌላቸው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

10. **"የበዓል ቀናት"** ማለት አግባብ ባለው ሕግ መደበኛ ሥራ እንዳይሰራባቸው የተለዩ ሐይማኖታዊና ብሔራዊ በዓላት ናቸው፤

11. **"የኮንስትራክሽን ማሽነሪ"** ማለት የተለያዩ የኮንስትራክሽን ስራዎችን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውሉ ማናቸውም ባለብረትም ሆነ ባለጎማ ማሽነሪዎች ነው፤

12. **"ግማሽ ተሣቢ"** ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪው ጭነትና ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤

13. **"ተሣቢ"** ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤

14. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ክልል በሚገቡና በከተማ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ እንዲሁም ከተማዋን አቋርጠው በሚያልፉ ከ1 ቶን ወይም ከ10 ኩንታል በላይ የመጫን አቅም ያላቸው የተለያዩ የፈሳሽና የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪዎች እና የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ዋና ድንጋጌዎች</u>

4. **<u>የሰዓት ገደብ ስለመወሰን</u>**

   1. ማንኛውም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እና የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ከጠዋቱ 1፡00 እስከ 3፡00 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 10፡30 እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ወደ ከተማ ውስጥ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ፣ ጭነት መጫንም ሆነ ማራገፍ እንዲሁም በዋና ዋናና የትራፊክ ፍሰት በሚበዛባቸው መንገዶች ላይ መቆም የተከለከለ ነው፤
   2. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ የተከለከለ የጭነት ተሽከርካሪ ወይም የኮንስትራክሽን

ማሽነሪ ወደ ከተማው ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ እያለ የሰዓት ገደቡ ቢደርስበት በከተማዋ መግቢያ በሮች ከዋና መንገድ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ላይ የአካባቢውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ በመቆም የሰዓት ገደቡ እስኪያልፍ መጠበቅ አለበት፤

3. ማንኛውም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ በከተማ ውስጥ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ በዚህ መመሪያ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ቢደርስበት የአካባቢውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ ከመንገድ በመውጣት መቆም አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለጸው ሰዓት ውጭ እንዲሁም እሁድ እና የበአል ቀናት ማናቸውም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወደ ከተማ ውስጥ መግባትም ሆነ በከተማ ውስጥ መንቀሳቀስ፣ ጭነት መጫን ሆነ ማራገፍ ይችላል፡፡

## 5. <u>የሰዓት ገደብ የማይመለከታቸው ተሽከርካሪዎች</u>

ከዚህ በታች የተገለፁት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በማንኛውም ሰዓት ወደ ከተማ መግባትም ሆነ መንቀሳቀስ ይችላሉ፤

**ሀ)** ሰሌዳቸው በሀገር መከላከያ ወይም በፖሊስ የተመዘገበ የሀገር መከላከያ እና ሌሎች የፀጥታ ስራዎችን የሚያከናወኑ ከባድና ቀላል የጭነት ተሽከርካሪዎች፤

**ለ)** በህግ መሠረት የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ተብለው የተለዩ የድንገተኛ አደጋ የሚሰሩ ቀላልና ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች፤

**ሐ)** ነዳጅ የሚያመላልሱ ቦቴዎች፤

## 6. <u>የባለሥልጣኑ ኃላፊነት</u>

ባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 84/2016 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. መመሪያውን በተለያዩ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ፤

2. በየከተማው መግቢያ ላይ የጊዜ ገደቡን በተመለከተ መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን የማስቀመጥ፤
3. ለመመሪያው ተግባራዊነት ተገቢውን ቁጥጥርና ድጋፍ የማድረግ፤
4. በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን በመፈፀም ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ መረጃ በማደራጀት የመያዝ፤

7. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ

**ሀ)** በተከለከለ ሰዓት ወደ ከተማ ውስጥ በመግባት በዋና ዋና መንገዶች ላይ ያቆመ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ይቀጣል፣

**ለ)** በዋና ዋና መንገድ ላይ የተንቀሳቀሰም ሆነ የጭነት መጫንና ማውረድ ተግባር የፈፀመ ወይም የኮንስትራክሽን ሥራ የሰራ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) ይቀጣል፣

**ሐ)** በዚህ መመሪያ የተደነገገውን ቅጣት በመተላለፍ ከተቀጣ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋቱን በመድገም የተገኘ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ቅጣት በእጥፍ ይቀጣል፤

2. በተከለከለው ሰዓት በከተማው ውስጥ ሲንቀሳቀስ በመገኘቱ ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ሰዓቱ ሳይደርስ የቅጣት ወረቀቱን ይዞ በተከለከለው ሰዓት እንዲንቀሳቀስ አይፈቀድለትም፤ የትራፊክ ተቆጣጣሪው ተሽከርካሪውን ፍሰት የማያሰናክል ቦታ ላይ እንዲቆም በማድረግ ቅጣቱን እንዲከፍል ማድረግ አለበት፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የቀመጠውን በመተላለፍ ሲንቀሳቀስ የተገኘ አሽከርካሪ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ትዕዛዝ ባለመፈፀም በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 395/2009 መሠረት ተጨማሪ ቅጣት ይጣልበታል፤
4. በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን በመፈፀም ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ መረጃ በሚመለከተው የስራ ክፍል ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

8. <u>የቅሬታ አቀራረብ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰደ እርምጃ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህ መመሪያ በአግባቡ እንዲፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጭነት፣ ማሽነሪዎችን እና መሰል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 38/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ቢሮው ያወጣው መመሪያ ወይም ሰርኩላር እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተገለጹት ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

11. <u>መመሪያውን ስለ ማሻሻል</u>

ቢሮው ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል፡፡

12. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በቢሮው ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ

ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ፤ የካቲት 2016 ዓ.ም

ምትኩ አስማረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ